## አዋጅ ቁጥር156/2010 ዓ/ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጤና አግልግሎትና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 75/2000 ዓ.ም ለማሻሻል የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ)

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 75/2000 ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት በተሻሻለዉ የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(3.1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አዉጥቷል።

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጤና አግልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር156/2010 ዓ/ም**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2

### ማሻሻያ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 75/2000 ዓ/ም እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡-

1. በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1(ለ) ሥር የተመለከተዉ ተሰርዞ "በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በሆስፒታሎች አማካኝነት የሚሰጥ የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ፣ የድህረ-ወሊድ እና የቤተሰብ ዕቅድ አግልግሎት" በሚለዉ ተተክቷል።
2. በአዋጁ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1(ሸ) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑሳን አንቀጾች ተጨምሯል፡-
   - (ቀ) እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናትን በመግደል የሚታወቁ ስድስት ዋና ዋና በሽታዎች ማለትም ወባ፣ተቅማጥ፣የሳንባ ምች፣ኩፍኝ፣ከባድ የጨቅላ ህጻን በሽታ እና ከፍተኛ የምግብ እጥረት በሽታ፣
   - (በ) ጨቅላ ህጻናት ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ እስከ ሃያ ስምንት ቀን ድረስ የሚያጋጥማቸዉ ማናቸዉም የጤና ችግር የህክምና አገልግሎት"
   - (ተ) ወጪያቸው በመንግስት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለክፊያ የሚሰጡ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች

## <u>አንቀጽ 3</u>

## <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት ከሀምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ

ሐምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም

አሻድሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ኘሬዚዳንት